ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA



# ለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ሰጪዎች የተዘጋጀ የቤተሰብ ዕቅድ የምክክር አገልግሎት አጋዥ ማጣቀሻ

# ምስጋና

ይህ የቤተሰብ እቅድ የምክክር አገልግሎት አጋዥ ማጣቀሻ የጤና ሚኒስቴር ከቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሌኒየም የሕክምና ኮሌጅ እና አጋር ድርጅቶች ባደረጉት ሙያዊ ድጋፍ የተዘጋጀ ሲሆን በዝግጅቱ ወቅት የክልል ጤና ቢሮዎች እና የቤተሰብ እቅድ ቴክኒካል ኮሚቴ ሙያዊ አስተያየቶችን በመስጠት ከፍተኛ አስተዋፆ አበርክተዋል፡፡ የጤና ሚኒስቴር አስተዋፆ ላበረከቱ አካላት ሁሉ ምስጋና ያቀርባል፡፡

**ዶ/ር መሰረት ዘላለም**

የእናቶች፣ ሕጻናትና አፍላ ወጣቶች ጤና አገልግሎት መሪ ስራ አስፈጻሚ

# ማውጫ

**መግቢያ** 6

**ክፍል 1፡ የተግባቦት ነጥቦች** 9

1. ግላዊ እና ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ አገልሎት 10
2. ተገልጋዮችን ማዳመጥ 12
3. የቤተሰብ ዕቅድ አማራጮች ላይ በዝርዝር መወያየት 14
4. ተገልጋዮች ስለ ጎንዮሽ ጉዳት ያላቸዉን ሃሳብ መወያየት 16
5. ያለምንም ጫና የተገልጋዮችን ምርጫ ማክበር 18
6. ተገልጋዮች የሚጠቀሙትን የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴ ለማቆም ሲወስኑ ያለምንም ጫና ዉሳኔያቸዉን ማክበር 20

**ክፍል 2፡ አራቱ “መ” ዎች - የቤተሰብ ዕቅድ የምክክር አገልግሎት መመሪያዎች** 23

# መግቢያ

ጥራት ያለው የቤተሰብ ዕቅድ የምክክር አገልግሎትን ማቅረብ የስነ-ተዋልዶ ጤና መብት እና ደህንነት ለማሻሻል ወሳኝ ሚና አለው። የቤተሰብ ዕቅድ ሴቶች ያልተፈለገ እርግዝናን እንዲከላከሉ ከመርዳቱም ባሻገር የእናቶችና እና የህጻናትን ጤና ያሻሽላል።

በአገር አቀፍ ደረጃ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የቤተሰብ ዕቅድ የምክክር አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ ከሚሰጥበት ጥራት በይበልጥ በ“Method Information Index Plus” መለኪያ መሰረት ማሻሻል እንደሚቻል ያመላክታሉ።

በኢትዮጵያ ዉስጥ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አገልግሎት ሰጪዎች (የጤና ባለሙያዎች) መመሪያዉ ከሚያዘዉ በተቃራኒ ተገልጋዮችን የረጅም ጊዜ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ የመጫን ወይም ዘዴዎቹን ለማቋረጥ እና ከሰዉነታቸዉ ለማውጣት ፈቃደኛ የማይሆኑበት ጊዜ እንዳለ ይጠቁማሉ።

ይህ አጭር የማጣቀሻ መፅሃፍ ከዚህ ቀደም በጤና ሚንስትር አገልግሎት ላይ የዋሉ የቤተሰብ ዕቅድ የስልጠና እና አተገባበር መመሪያዎችን ለመደገፍ የተዘጋጀ ሲሆን በጥቅም ላይ ያሉትን የሚተካ አይደለም። ማጣቀሻው በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ነዉ።

ክፍል 1 የቤተሰብ ዕቅድ የምክክር አገልግሎትን ጥራት እና የተጠቃሚዎችን እርካታ ለማሻሻል የሚያግዙ የተግባቦት ነጥቦች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

ክፍል 2 በቤተሰብ እቅድ የምክክር ሂደቶች ማለትም መግባባት፣ መጠየቅ፣ መወያየት ፣መወሰን እና መተግበር (Rapport Building, Explo- ration, Decision making, and Implementation (REDI) መመሪያዎች ዉስጥ (አራቱን “መ” ዎች) በአጭሩ ያስቀምጣል፡፡

የቤተሰብ ዕቅድ የምክክር አገልግሎት ማለት በአገልግሎት ሰጪዎች እና በተገልጋዮች መካከል በቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች ላይ የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ እንዲሁም ተገልጋዮች ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ የሚደረግ እገዛን ያጠቃልላል፡፡ እገዛዎቹም በተገልጋዮች ፍላጎት እና ምርጫ ላይ ተመስርቶ አማራጭ ዘዴዎች መምረጥ፣ መጠቀም ፣ መቀየር እና ማቋረጥን ያካትታል፡፡

# ክፍል 1

## የተግባቦት ነጥቦች

# የትኩረት ነጥብ 1

## ግላዊ እና ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ አገልግሎት



**ለምን አስፈለገ?**

ሁሉንም የቤተሰብ ዕቅድ የምክክር ክፍለ ጊዜዎች ግላዊ እና ሚስጥራዊነታቸው የተጠበቀ ማድረግ፣ ተገልጋዮች በአገልግሎቱ ላይ ያላቸው እምነት እንዲጨምር እንዲሁም ጠቃሚ ግላዊ መረጃዎችን በግልጽ ለአገልግሎት ሰጪዎች እንዲያጋሩ ያበረታታል፡፡

# ቁልፍ መልዕክት፡

- የአገልግሎት መስጫ ክፍሉን በር በሚገባ ይዝጉ
- የአገልግሎት መስጫ መስኮት/መጋረጃ ይዝጉ
- በሌሎች ፊት ተገልጋዮችን ግላዊ ጥያቄዎችን አይጠይቁ
- ለተገልጋዮች የግል መረጃቸዉ በሚስጥር እንደሚያዝ ያረጋግጡ
- ከራሳቸው ከተገልጋዮች ፈቃድ ውጪ የግል መረጃቸውን ለማንም እንደማያጋሩ አስረግጠዉ ይንገሯቸው



# የትኩረት ነጥብ 2

## ተገልጋዮችን ማዳመጥ



### ለምን አስፈለገ?

የቤተሰብ እቅድን በተመለከተ የተገልጋዮችን አመለካከት እና ሀሳብ በዝርዝር መጠየቅ ምርጫቸውን አውቆ ለማክበር እንዲሁም ግንዛቤያቸውን ለማስፋት ይረዳል፡፡

# ቁልፍ መልዕክት፡

- የተገልጋዮችን ፍላጎት በራስዎት ከመገመት ይቆጠቡ
- ተገልጋዮችን የሚያወያይ ጥያቄ ይጠይቁ
- ተገልጋዮች ያላቸውን ስጋት እንዲያጋሩ ያበረታቱ
- ተገልጋይ በክፍል ውስጥ እያለ የስልክ ጥሪ አይቀበሉ/ አያድርጉ ወይም የፅሑፍ መልዕክት አይላኩ ለተገልጋዮች ርህራሄና ችግራቸዉን ለመረዳት ፍላጎት እንዳለዎት በገፅታዎ ያሳዩ ፥ የሚናገሩት ነገር ስህተት ሊሆን ይችላል የሚል ስሜት እንዳይሰማቸው ጥንቃቄ ያድርጉ ተገልጋዮችን አጽንዖት ሰጥተው እያዳመጧቸው መሆኑን ለማሳየት ያጋሩትን መረጃ መልሰው በራስዎት አባባል ይድገሙላቸው
- ለውይይት የሚጋብዝ ገጽታ ያሳዩ፡፡ ለምሳሌ፡- ፈገግታ

ወይም ተገልጋዮችን ፊት ለፊት እያዩ ማነጋገር

- የችኮላ ምልክት አያሳዩ እንዲሁም ከምክክሩ ውጭ የሆነ ተጨማሪ ስራ አይስሩ
- ተገልጋዮች ውሳኔ እንዲወስኑ በቂ ጊዜ ይስጡ



# የትኩረት ነጥብ 3

## የቤተሰብ ዕቅድ አማራጮች ላይ በዝርዝር መወያየት



### ለምን አስፈለገ ?

ሚዛናዊነቱን በጠበቀ መልኩ ሁሉንም ተስማሚ የሆኑ የቤተሰብ እቅድ ዘዴዎችን መግለጽ ተገልጋዮች ለራሳቸው በተሻለ መልኩ የሚሆናቸውን ዘዴ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡

# ቁልፍ መልዕክት፡

- • ተገልጋዮች ለራሳቸው ይሆነናል ብለው ካሰቡት የቤተሰብ እቅድ ዘዴ በተጨማሪ አማራጭ ዘዴዎች ላይ ለመመካከር ጥያቄ ያቅርቡላቸዉ
- ለተገልጋዮች ያሉትን የቤተሰብ እቅድ ዘዴ አማራጮች በመዘርዘር ለእነርሱ የጤና ሁኔታ ምቹ ያልሆኑ ዘዴዎች ካሉ እንዲለዩ ያግዟቸው
- ተገልጋዮች ይስማማናል ብለው ስለመረጡት ዘዴ ዝርዝር መረጃ ይስጧቸው
- በቀጥታ እና በግልፅ በመናገር ተገልጋዮች የተሰጣቸውን መረጃ በትክክል እንደተረዱ ያረጋግጡ



# የትኩረት ነጥብ 4

## የጎንዮሽ ጉዳት ላይ መወያየት



**ለምን አስፈለገ ?**


ተገልጋዮች በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ የቤተሰብ እቅድ ዘዴዎች ሊኖራቸው ስለሚችል የጎንዮሽ ጉዳት መረጃ ያስፈልጋቸዋል፡፡ እነዚህ የጤና ለውጥ ስጋቶች ላይ አስቀድሞ ምክክር ካልተደረገ ብዙ ተገልጋዮች የጎንዮሽ ጉዳት ሲያጋጥማቸው የቤተሰብ እቅድ ዘዴውን መጠቀም ሊያቆሙ ይችላሉ፡፡

## ቁልፍ መልዕክት፡

- ተገልጋዮችን ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳት በተመለከተ በቂ እና ሚዛናዊ መረጃ ይስጡ
- የትኞቹ የጎንዮሽ ጉዳቶች የሚጠበቁ እና መጠነኛ እንዲሁም የትኞቹ የከባድ ህመም ምልክት እንደሆኑ ለይተው ያብራሩ
- ለተገልጋዮች የወር አበባ መዛባት ሊያጋጥም እንደሚችል ያስረዱ ፤ በዚህም ላይ ከተገልጋዮች ጋር ውይይት ያድርጉ
- የትኛውንም የቤተሰብ እቅድ ዘዴ መጠቀም የቤት ውስጥ ስራዎችን ከመስራትና እና ሌሎች

እንቅስቃሴዎችን ከማድረግ እንደማያግድ በግልጽ ያስረዱ

- ተገልጋዮች ያላቸውን ማንኛውንም አይነት ቅሬታ ለመረዳት ጥያቄ ይጠይቋቸው እንዲሁም ምላሻቸውን በጥሞና ያድምጡ
- ተገልጋዮች ያላቸውን ስጋትና የተሳሳተ ግንዛቤ አሉባልታ ነው ብለው አያጣጥሉ ይልቁንም ትክክለኛውን መረጃ በመስጠት ውይይት ያድርጉ



# የትኩረት ነጥብ 5

## ያለምንም ተፅኖ የተገልጋዮችን ምርጫ ማክበር



**ለምን አስፈለገ ?**


ተገልጋዮች በፈቃዳቸው በመረጃና እውቀት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ መርዳት ጥራት ያለው የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ለማቅረብ ወሳኝ ሚና አለው። በማንኛዉም ምክንያት ተገልጋዮች ያልመረጡትን የቤተሰብ እቅድ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ ተፅዕኖሊደረግባቸዉ አይገባም። ይህ ተፅዕኖ የተገልጋዮችን የግል ምርጫ የሚፃረር ከመሆኑም በላይ ተገልጋዮች በምክክር አገልግሎቱ ላይ ያላቸውን እምነት ሊያሳጣ ይችላል።

# ቁልፍ መልዕክት፡

- ተገልጋዮች መጠቀም ያለባቸውን የቤተሰብ እቅድ ዘዴ በራስዎት ወስነዉ አይንገሯቸዉ፤ ተገልጋዮች በግል ሁኔታቸው ወይም ምርጫቸው ላይ ተመርኩዘው እንዲወስኑ ያበረታቷቸዉ ፤ክርን የቆዳ ስር የሚቀመጥ ወይም በማህፀን ውስጥ የሚቀመጥ የቤተሰብ እቅድ ዘዴን ለመጠቀም ተገልጋዮች ብቁ ቢሆኑም እንኳን ለሁሉም

ተገልጋዮች ተመራጭ የማይሆንበት አጋጣሚ እንዳለ እንዲረዱ ማድረግ

- ተገልጋዮች የሚፈልጉት የቤተሰብ እቅድ ዘዴ ለመምረጥና ለመወሰን ተጨማሪ ጊዜ ሊያስፈልጋቸው እንደሚችል ያስታውሱ



# የትኩረት ነጥብ 6

## ተገልጋዮች የሚጠቀሙትን የቤተሰብ ዕቅድ ለማቆም ሲወስኑ ያለምንም ተጽኖ ዉሳኔያቸዉን ማክበር



**ለምን አስፈለገ ?**


ተገልጋዮችእየተጠቀሙትባለው የቤተሰብ እቅድ ዘዴ ደስተኛ ካልሆኑ ወይም መጠቀም ማቆም ከፈለጉ እንዲቀይሩ ወይም እንዲያቋርጡ መርዳት ጥራት ላለው የምክክር አገልግሎት አስፈላጊ ነው፡፡ ማንኛውም ምክንያት ተገልጋዮች አንድን የቤተሰብ እቅድ ዘዴ እንዲጠቀሙ ተፅዕኖ ሊደረግባቸዉ አይገባም፡፡ ይህ ተፅዕኖ የተገልጋዮችን የግል ምርጫ የሚፃረር ከመሆኑም በላይ ተገልጋዮች አገልግሎቱ ላይ ያላቸውን እምነት ሊያሳጣ ይችላል፡፡

## ቁልፍ መልዕክት፡

- ተገልጋዮች እየተጠቀሙበት ባለው የቤተሰብ እቅድ ዘዴ ደስተኛ ካልሆኑ ያላቸውን ስጋት ለመቅረፍ ይሞክሩ ወይም ሌሎች አማራጮች ላይ ይወያዩ
- ተገልጋዮች በሚጠቀሙበት የቤተሰብ እቅድ ዘዴ ደስተኛ እንዳይሆኑ ያደረጋቸውን ምክንያት በማወቅ ችግሩ በህክምና እርዳታ ወይም በሌሎች ቅድመ

ጥንቃቄዎች ሊቀረፍ የሚችል መሆኑን ያጣሩ

- ተገልጋዮች እየተጠቀሙበት ያለውን የቤተሰብ እቅድ ዘዴ መጠቀም ከጀመሩ አጭርም ሆነ ረጅም ጊዜ ቢሆን ከምክክር በኋላ ዘዴው ከሰውነታቸው እንዲወጣላቸው ወስነው ሲጠይቁ ሁሌም ፈቃደኛ ይሁኑ
- ተገልጋዮችን ያለፍላጎታቸው አንድን የቤተሰብ እቅድ ዘዴ እየተጠቀሙ እንዲቀጥሉ አይጫኗቸው



# ክፍል 2

## በቤተሰብ እቅድ አራቱ የ “መ” የምክክር አገልግሎት ሂደቶች

**አንድ፡** መግቢያ እና ትውውቅ
**ሁለት፡** መመርመር/መጠየቅ/መወያየት
**ሶስት፡** መወሰን
**አራት፡** መተግበር

አራቱ የ “መ” ምክክር ሂደቶችን በተመለከተ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ለማግኘ የቤተሰብ ዕቅድ የምክክር አገልግሎት ላይ በጤና ሚኒስቴር የተዘጋጀውን የስልጠና መመሪያ ይመልከቱ።

# ሂደት 1
## መግቢያ እና ትውውቅ

1. ለተገልጋዮች የአክብሮት ሰላምታ ይስጡ
2. የተገልጋዮችን አይነት ይለዩ (አዲስ፣ በተሰጣት አገልግሎት ደስተኛ የሆነች ተመላሽ ተገልጋይ ፣ በተሰጣት አገልግሎት ደስተኛ ያልሆነች ተመላሽ ተገልጋይ)
3. የምክክር አገልግሎቱ በግል፣ ሌሎች ሰዎች በማያዩበትና በማይሰሙበት ሁኔታ እንደሚሆን እንዲሁም መረጃው በምስጢር እንደሚያዝ ያረጋግጡ
4. የተገልጋዮች የግል እና ሚስጥራዊ መረጃዎች ላይ መወያየት አስፈላጊ መሆኑን ይረዱ
5. በሁሉም የምክክር ሂደቶች ላይ ጥሩ የመግባቢያ ክህሎቶችን ይተግብሩ(በጥሞና ማዳመጥ፣ ተገልጋዮች የተናገሩትን ግልጽ ለማድረግ ያሉትን መልሶ መድገም፣ ማበረታታት እና ማሞገስ)



## ሂደት 2

### መመርመር/መጠየቅ/መወያየት

ተገልጋዮች ወደ ጤና ተቋሙ የመጡበትን ምክንያት ይለዩ (ይህን ማወቅ የተገልጋዮችን የምክክር አገልግሎት ፍላጎት ለመለየት ይረዳል)

2. የተገልጋዮችን የወደፊት የስነ-ተዋልዶ እቅድ፣ ከዚህ በፊት የነበራቸውን ልምድ እና የአሁን ሁኔታቸውን ይጠይቁ

ሀ. የስነ-ተዋልዶ ልምድ አና እቅድ፤ ስለ ጤናማና አመቺ የመውለጃ ጊዜ እና አራርቆ ስለመውለድ

ለ. ማህበራዊ የግንኙነት ሁኔታ ሐ. ስነ-ጾታ

ሐ. ከዚህ በፊት ኤች.አይ.ቪን ጨምሮ በግብረ- ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ የአባላዘር በሽታዎች ተይዘው እንደነበር ያጣሩ ፣ የወደፊት የመያዝ እድልንና፣ እርግዝናን ስለ መከላከል በማስረዳት፣ ተገልጋዮች በነዚህ በሽታዎች የመያዝና በሽታውን የማስተላለፍ እድላቸውን እንዲገነዘቡ ያድርጉ።

3. ተገልጋዮች ውሳኔ ለመወሰን እንዲረዳቸው ለኤች. አይ.ቪ እና ሌሎች አባላዘር በሽታዎች ያላቸውን ተጋላጭነት እንዲሁም ያላቸውን የጾታዊ ግንኙነት ልምድና ሌሎች ስነ-ጾታዊና ማሕበራዊ ጉዳዮችን ይመርምሩ

ሀ. የጾታዊ ግንኙነት ልምድ

ለ. ውሳኔ ለመወሰን የሚረዱ ማሕበራዊ እና ስነ-ጾታዊ ሁኔታዎች

ሐ. ለኤች አይ ቪ እና ሌሎች አባላዘር በሽታዎች ያላቸውን ተጋላጭነት

4. ውይይቱን የተገልጋዮች ፍላጐት ላይ ያተኮረ እንዲሆን ያድርጉ ፣ የሚመርጡት የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴ ካለ ይጠይቁ ፤ ከሌለ ሌሎች ተስማሚ ዘዴዎችን ይዘርዝሩ፣እንዲሁም አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት የተሳሰቱ ግንዛቤዎችን ያርሙ


5. እርግዝና አለመፈጠሩን ያረጋግጡ፣ የወር አበባ ፍሰት ለውጥ ካለ እንዲኖር ያደረጉ ምክንያቶች እና በቅርብ የተከሰተ እርግዝና እና ሌሎች የጤና እክሎች አለመኖራቸውን ያረጋግጡ

# ሂደት 3

## መወሰን

ተገልጋዮች ምርጫቸውን እንዲወስኑ ወይም በመረጡት ዘዴ እርግጠኛ እንዲሆኑ ያግዟቸው።(በአገልግሎቱ ደስተኛ ሆነው የተመለሱ ተገልጋዩች ከሆኑ ሌሎች ተጨማሪ አገልግሎቶችን ይፈልጉ እንደሆን ይጠይቁ። ካልፈለጉ ወደ ሂደት 4 ቁጥር 5 ይቀጥሉ)

1. ለእያንዳንዱ ውሳኔ አግባብ ያላቸው አማራጮችን አቅርቢ/ብ
2. ተጋልጋዮች እያንዳንዱ አማራጭ ያለውንና ሊያስከትል የሚችለውን ጠቀሜታ እና ጉዳት እንዲያመዛዝኑ ድጋፍ ያድርጉላቸዉ (የግንዛቤ ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል መረጃ ይስጧቸው)
3. ተገልጋዮች የራሳቸዉ ዉሳኔ እንዲወስኑ ያበረታቱ



# ሂደት 4
## መተግበር

1. ተገልጋዮች የወሰኑትን የቤተሰብ እቅድ እንዲተገብሩ የሚረዱ ዝርዝር እቅዶችን እንዲያዘጋጁ ይርዷቸው (የቤተሰብ እቅድ ዘዴውን ማግኘትና መጠቀም፣ በግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን መቀነስ፣ ካልተፈለገ እርግዝና መከላከል እና ሌሎችም በረጃዎች ይስጡ)
2. ተገልጋዮች የመረጡትን ዘዴ በአግባቡ እንዲጠቀሙና ክህሎት እንዲኖራቸው ያግዟቸው
3. ተገልጋዮች ለመጠቀም የወሰኑትን ዘዴ ከመጠቀም ሊያግዳቸው የሚችል እንቅፋት ካለ ይለዩ
4. እነዚህን እንቅፋቶች ለማለፍ መፍትሄ ያቅርቡ
5. እንደ አስፈላጊነቱ ተከታታይ እቅድ ያዘጋጁ ወይም ወደ ሌላ ተጨማሪ አገልግሎት ይምሯቸው

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

የዜጎች ጤና ለሃገር ብልጽግና!
HEALTHER CITIZENS FOR PROSPEROUS NATION!